# የኮቪድ-19 ክትባቶች እና የተዋልዶ ጤና
## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

Vaccinate WA
CovidVaccineWA.org

የ ኮቪድ-19 ክትባቶች እንዴት ስነተዋልዶላይ ተፅዕኖ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ስጋቶች መኖራቸው የተለመደ ነው። የ Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት) አሁን ለማርገዝ የሚሞክሩትን ወይም ወደፊት ማርገዝ የሚችሉትን ጨምሮ ኮቪድ-19 ክትባቶችን ዕድሜያቸው 6 ወራት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሁሉ ይመክራል። በአሁኑ ጊዜ የኮቪድ-19 ክትባቶችን ጨምሮ ማንኛቸውም ክትባቶች አሁንም ሆነ ወደፊት የመራባት ችግሮችን እንደሚያስከትሉ የሚያሳይ ምንም ማረጋገጫ የለም።

አንዳንድ አንባቢዎች ከዚህ ቀደም ከመራባት ጋር በተደረጉ ትግሎች፣ በቀለም ሰዎች ላይ በደረሰው የዘረኝነት አያያዝ ታሪካዊ ትራዉማ፣ ወይም በሕክምና መስክ ውስጥ በሚከሰቱ የሴቶች/ትራንስ ወንድ እና ሴት/በጾታ የማይስማሙ ሰዎች አጠቃላይ የጤና ቅሬታዎች ምክንያት በዚህ ሰነድ ውስጥ ለተካተቱት ርዕስ ጉዳዮች ስሜታቸው ሊነካ ይችላል።

**ስለ ኮቪድ-19 ክትባት እና ስለ ተዋልዶ ጤና ስለሚጠየቁ አንዳንድ የተለመዱ ጥያቄዎች መልስ ለማወቅ ከታች ይመልከቱ ።**

### ጥያቄ፡- ልጅ የመውለድ ችሎታዬ በኮቪድ-19 ክትባት ይጎዳል?

**መልስ፡-**

በአሁኑ ጊዜ የኮቪድ-19 ክትባቶችን ጨምሮ ማናቸውም ክትባቶች በሴቶችም ሆነ በወንዶች ላይ የመራባት ችግር እንደሚያስከትሉ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም። ክትባቶቹ ኮሮናቫይረስን ለመዋጋት ከሰውነት በሽታ የመከላከል ስርዓትዎ ጋር የሚሠሩ ሲሆን በስነተዋልዶ አካላትዎ ላይ ጣልቃ አይገቡም። በኮቪድ-19 ክትባቶች ክሊኒካዊ ሙከራዎች እና ለመፀነስ በሚሞክሩ ባለትዳሮች ላይ በተደረገ ትልቅ ጥናት ውስጥ፣ የማርገዝ መጠን የኮቪድ-19 ክትባቶች ለሚወስዱት እና ክትባቶቹን ለማይወስዱት ተመሳሳይ ነበር። የኮቪድ-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ውጤታማ ናቸው። Centers for Disease Control and Prevention (CDC)፣ American College of Obstetricians and Gynecologists (ACOG፣ የአሜሪካ የፅንስና የማህፀን ሐኪሞች ኮሌጅ)፣ እና Society for Maternal-Fetal Medicine (SMFM፣ የእናቶች ማህበር -የፅንስ መድሃኒት) ለእርጉዝ፣ ለሚያጠቡ ወይም ለማርገዝ ላሰቡ ሰዎች የኮቪድ-19 ክትባትን ይመክራሉ።

የኮቪድ ክትባት ለምን እንደሚመከር ከዶክተር LaSalle ለመስማት ይህንን ሊንክ ይጎብኙ፡- ስነተዋልዶ እና የኮቪድ-19 ክትባቶች - YouTube

### ጥያቄ፡- ክትባቱ የወር አበባ ዑደቴን ይለውጣል?

**መልስ፡-**

ለኮቪድ-19 ከተከተቡ ሰዎች የተወሰነ ክፍል ከተከተቡ በኋላ የወር አበባ ዑደታቸው ላይ ለውጦች መኖራቸውን፣ ለምሳሌ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ የወር አበባ፣ በወር አበባ መካከል አጭር ክፍተቶች መኖር ወይም ከወትሮው የበለጠ ከባድ ደም መፍሰስን ሪፖርት አድርገዋል። በ 2022 በተደረገ ጥናት ውስጥ፣ የወር አበባ ላይ እያሉ የኮቪድ-19 ክትባት የወሰዱ ሰዎች፣ በክትባታቸው ወቅት በወር አበባቸው ዑደት ላይ ከአንድ ቀን ያነሰ ጭማሪ እንዳሳዩ ተረጋግጧል። የአንድ ቀን ልዩነት በተለመደው የወር አበባ ዑደት መለያየት ውስጥ ነው። በወር አበባ ዑደት ውስጥ እነዚህ ሊከሰቱ የሚችሉ ጊዜያዊ ለውጦች ቢኖሩም፣ **የኮቪድ-19 ክትባቶች የስነተዋልዶ ችግርን እንደሚያስከትሉ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም**። የዑደትዎ ለውጥ የእቁሌሽን ጊዜን ሊለውጥ ይችላል። የተፈጥሮ የቤተሰብ ምጣኔ እና ሌሎች በዑደት ክትትል ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች፣ እቁሌሽንን ለመለየት እና እርግዝናን ለማስወገድ/ለማቀድ የበለጠ ይከብዳቸዋል። ስለ ዑደትዎ ለመወያየት እና ስለቤተሰብ ምጣኔ የበለጠ ለማወቅ ከአገልግሎት አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።

### ጥያቄ፡- የኮቪድ-19 ክትባት የወሊድ መቆጣጠሪያን ሊጎዳ ይችላል?

**መልስ፡-**

በ Planned Parenthood መሠረት፣ የኮቪድ-19 ክትባት የወሊድ መቆጣጠሪያን የበለጠ ወይም ያነሰ ውጤታማ እንደሚያደርግ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም። በአሁኑ ጊዜ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የወሊድ መቆጣጠሪያቸው ሥራ ማቆሙን ከተከተቡ ሰዎች የተሰጠ ሪፖርት የለም። የወር አበባ ዑደት ለውጦች ሪፖርቶች ቢኖሩም፣ ይህ የአንድን ሰው የወሊድ መቆጣጠሪያ ሥራን አይጎዳም። ይህ የወር አበባ ዑደቶችን እና የእቁሌሽን ጊዜያትን ለመከታተል ችግር ሊፈጥር ይችላል፤ እንደ የወሊድ እውቀት ዘዴ ያሉ ተፈጥሯዊ የወሊድ መቆጣጠሪያዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች የእቁሌሽን ጊዜያቸውን ማወቅ ሊከብዳቸው ይችላል። ግለሰቦች እቁሌሽናቸውን እንዲከታተሉ የሚያግዙ መሳሪያዎች አሉ። ስለ አማራጮችዎ እና የበለጠ ለማወቅ ከአቅራቢዎ ጋር እንዲነጋገሩ ይመከራል።

## ጥያቄ፡- ክትባቱ የወንድ ዘር ፈሳሽ ላይ ተጽዕኖ አቅም ማነስን ሊያስከትል ይችላል?

**መልስ፡-**

የትኛውም ክትባቶች የኮቪድ-19 ክትባቶችን ጨምሮ የወንድ የመራቢያ አካላት ችግሮች ያለባቸውን በዚህ ጊዜ የመጉዳት ወይም የአቅም የማነስ ችግር እንደሚፈጥር የሚያሳይ ምንም አይነት መረጃ የለም። mRNA የኮቪድ-19 ክትባት በወሰዱ 45 ጤናማ ወንዶች ላይ በቅርብ የተደረገ አነስተኛ ጥናት  እንደ መጠን እና እንቅስቃሴ ያሉ ከክትባቱ በፊት እና በኋላ የነበሩ የወንድ የዘር ባህሪያትን ተመልክቷል። ተመራማሪዎቹ ከክትባት በኋላ በእነዚህ የወንዴ ዘር ባሕርያት ላይ የጎላ ለውጥ አላገኙም። በአማራጭ፣ አንድ ጥናት የኮቪድ-19 ኢንፌክሽን ከበሽታው በኋላ ለወንዶች እስከ 60 ቀናት ድረስ ከመውለድ ብቃት መቀነስ ጋር ሊያያዝ እንደሚችል አረጋግጧል። በማንኛውም በሽታ የሚመጣ ትኩሳት እና የተለመደው የኮቪድ-19 ምልክት፣ የወንዱ የዘር ፍሬ ምርት ለአጭር ጊዜ እንዲቀንስ ሊያደርጉ ይችላሉ። ምንም እንኳን ትኩሳት የኮቪድ-19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳት ሊሆን ቢችልም፣ ከኮቪድ-ክትባት በኋላ ያለው ትኩሳት የወንድ የዘር ፍሬን እንደሚጎዳ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም። ተጨማሪ ስጋቶች ካሉዎት ከአቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።

## ጥያቄ፡- ክትባቱ የ IVF (In Vitro Fertilization) ህክምናዎችን ይጎዳል?

**መልስ፡-**

የኮቪድ-19 ክትባቱ በአይ IVF ህክምናዎች ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ያሉትን ውጤቶች እንደሚጎዳ የሚጠቁም ምንም ማስረጃ የለም። ጥናቶች የኮቪድ-19 mRNA ክትባት በ IVF የስኬት መጠኖች ላይ የሚያመጣውን ምንም ተጽዕኖ አላገኙም። አንድ ጥናት ክትባት የተከተቡ እና ያልተከተቡ ሲነጻጸሩ፣ ለአቫሪ ማነቃቂያ በሚሰጥ ምላሽ፣ በእንቁላል ጥራት፣ በፅንስ እድገት ወይም በእርግዝና ውጤቶች ላይ ምንም የጎላ ልዩነት አላገኘም። የኮቪድ-19 ክትባቶች ወሊድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ወይም ለመፀነስ ለሚታገሉት የበለጠ ችግር የሚፈጥሩ ሆነው አልተገኙም። እንደ ጉንፋን፣ ቴታነስ እና ዲፍቴሪያ ያሉ ብዙ ክትባቶች በእርግዝና ወቅት እና ከእርግዝና በፊት፣ በመደበኛነት ደህንነቱ በተረጋገጠ ሁኔታ ይሰጣሉ። የኮቪድ-19 ክትባት ለማርገዝ የሚሞክሩትንም ጨምሮ ዕድሜው 6 ወራት እና ከዚያ በላይ ላለ ለማንኛውም ሰው የሚመከር ነው።

## ጥያቄ፡- የኮቪድ-19 ክትባት የፅንስ መጨንገፍን ሊያስከትል ይችላል?

**መልስ፡-**

አይ፣ የኮቪድ-19 ክትባት ከእርግዝና በፊት፣ በእርግዝና ወቅት እና በኋላ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። የኮቪድ-19 ክትባቶችን መውሰድ የፅንስ መጨንገፍ አደጋን እንደሚጨምር የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም። ለኮቪድ-19 በተከተቡ ሰዎች ላይ ከፍ ያለ የፅንስ መጨንገፍ አልተገኘም። ሰዎች ከሚያስቡት በላይ የፅንስ መጨንገፍ መጠን ከፍ ያለ ሲሆን፣ ከ 10 እስከ 20 በመቶ የሚሆነው እርግዝና በፅንስ መጨንገፍ ያበቃል። አንዳንድ የተከተቡ ሰዎች የፅንስ መጨንገፍ ሊያጋጥማቸው ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ከክትባቱ ጋር የተገናኘ አይደለም - የክትባት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን የፅንስ መጨንገፍ ሊከሰት ይችላል። በእርግጥ በእርግዝና መጀመሪያ ላይ ከባድ የኮቪድ-19 ኢንፌክሽን ያጋጠማቸው ሰዎች የፅንስ መጨንገፍ እድላቸው ከፍ ያለ ነው። ክትባቱ ለእርስዎ እና ለልጅዎ ምርጥው የኮቪድ-19 መከላከያ ነው።

## የመረጃ ምንጮች


Centers for Disease Control and Prevention, “COVID-19 Vaccines for People Who Would Like to Have a Baby”. 2022. ኦንላይን በዚህ ይገኛል፡- COVID-19 Vaccines for People Who Would Like to Have a Baby | CDC

American College of Obstetricians and Gynecologists, ‘COVID-19 Vaccination Considerations for Obstetric-Gynecologic Care”. 2022. ኦንላይን በዚህ ይገኛል፡- COVID-19 Vaccination Considerations for Obstetric–Gynecologic Care | ACOG

World Health Organization, “Questions and Answers: COVID-19 vaccines and pregnancy.” 2022. ኦንላይን በዚህ ይገኛል፡- Questions and Answers: COVID-19 vaccines and pregnancy (who.int)

Mount Sinai, “Large Study Provides Reassurance that COVID-19 Vaccination Does Not Affect Fertility or Early Pregnancy.” 2022. ኦንላይን በዚህ ይገኛል፡- Large Study Provides Reassurance that COVID-19 Vaccination Does Not Affect Fertility or Early Pregnancy | Mount Sinai - New York


*በግል የሕክምና ውሳኔዎች ላይ ሁል ጊዜ ከታመነው የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎ ጋር ይማከሩ።*



ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ኢሜይል ወደ civil.rights@doh.wa.gov ይላኩ።